


**Junior, un nouvel ami**
Belotie Nkashama, QueenMama (ill.)
Editions Beth Story, 2021

Amharique
አማርኛ

| | | |
|---|---|---|
| **(Couver-ture)** | **Junior**<br>**Un nouvel ami**<br>Une histoire et un jeu | **ጁኒየር**<br>**አዲስ ጓደኛ**<br>ታሪክ እና ጨዋታ |
| (4ème de couver-ture) | Trois petits amis sont fous de joie de voir leur ville toute blanche et font un bonhomme de neige. De la maison voisine, Arthur, un nouveau dans le quartier, les observe. Il paraît qu'il a un serpent, disent les enfants… Aïe, comment pourront-ils s'entendre ? Grâce aux mikatés, un vrai délice ! | ሶስት ትንንሽ ጓደኛማቾች ከተማቸው የበረዶ ካባ ለብሶ በማየታቸው በጣም ተደስተዋል እና የበረዶ ሰው እየሰሩ ነው ። ከጎረቤት ቤት፣ ለአካባቢው አዲስ መጤ የሆነው፣ አርቱር ፣ እነርሱን ይመለከታቸዋል። "እባብ አለው ይባላል ...ኧረ እንዴት ይግባባሉ?" ይባባላሉ ልጆቹ ....እድሜ ለ ሚካቴ ፣ ፍፁም ጣፋጭ! |
| (p. 5) | Belotie Nkashama<br>Illustrations : QueenMama | ቤሎሲ ንካሻማ<br>ስነ ስዕላዊ ምሳሌዎች: ኩዊንማማ |
| | Junior<br>un nouvel ami | ጁኒየር<br>አዲስ ጓደኛ |
| | Éditions Bethstory | የቤተ ስቶሪ እትሞች |
| (p. 7) | Il a beaucoup neigé durant la nuit. La ville entière est recouverte d'un grand manteau blanc. Junior sort de la maison et s'empresse de rejoindre ses amis.<br>– Et si on faisait un bonhomme de neige ? propose alors Dino, vêtu d'une combinaison bleue.<br>– Ah oui ! Le plus grand qu'on n'ait jamais fait ! répond Junior. | ሌሊቱን ሙሉ በጣም ብዙ በረዶ ጣለ። ከተማዋ በሙሉ በታላቅ ነጭ ካባ ተሸፍናለች። ጁኒየር ከቤት ወጥቶ ከጓደኞቹ ጋር ለመቀላቀል ቸኩሏል።<br>"የበረዶ ሰው ብንሰራስ?" ዲኖ ሰማያዊ ጃምፕሱት የለበሰው ብሎ ጠየቃቸው።<br><br>"አ -- አዎ ! ከእስካሁን ከሰራነውየሚበልጥ ትልቅ!" ጁኒየር መለሰ ። |

(p. 8)

– Je vais chercher des branches pour lui faire des longs bras ! s’exclame Dino.
– On pourrait aller chercher des châtaignes pour lui faire des boutons.
– Oui, bonne idée Nina ! Et moi, je vais demander une carotte à ma maman pour lui faire un joli nez, ajoute Junior.

“ረጅም ክንዶች እንዲኖሩት ቅርንጫፎችን ፈልጌ መጣሁ! ” አለ ዲኖ ።
“ ለደረት ቁልፎች መስሪያ የሚሆኑ የሻቴኝ ፍሬ እንፈለግ ።”
“አዎ፣ በጣም ጥሩ ሃሳብ ኒና ! እኔ ደሞ፣ ቆንጆ አፍንጫ ለመስራት እናቴን ሄጄ ካሮት እለምናታለው፣ ” ቀጥሎ ጁኒየር አለ።

(p.10)

– Oh ! Regardez ! C’est le nouveau voisin ! s’écrie Junior.
– Mon frère dit qu’il a un grand serpent comme animal de compagnie. Tssssss, fait Dino, imitant ainsi le sifflement du reptile tout en rampant sur la neige, ce qui ne manque pas de faire rire Nina.
– On peut lui proposer de venir jouer avec nous ? demande Junior.
– Euh, non, il n’a pas vraiment l’air gentil, dit Nina, inquiète.

“ኧረ! እዩትማ! አዲሱ ጎረቤታችን ነው ! ” ብሎ ጁኒየር ጮኸ ።
“ ወንድሜ እቤቱ ውስጥ ትልቅ እባብ እንዳለው ያወራል ። ስስስስስ፣” ዲኖ በበረዶ ላይ እየተሳበ ተሳቢ እንስሳዎችን ጩኸት በማስመሰል ይላል፣ ይህም ኒናን ሳያስቃት አላለፈም።
“መጥቶ ከእኛ ጋር እንዲጫወት ልንጠይቀው እንችላለን?" ጁኒየር ጠየቀ።
ኒና በጭንቀት “ኧረ አይሆንም እሱ በጣም ጥሩ ልጅ አይመስልም" አለች።

(p. 12)

À peine Nina a-t-elle fini de parler que Junior fait signe de la main au petit voisin.
– Veux-tu jouer avec nous ?
– Non ! De toute façon, les bonshommes de neige sont pour les bébés, lâche le petit garçon en s’en allant tout penaud, les mains dans les poches.

ንግግሯን ከአፏ ላይ ሳትጨርስ ጁኒየር ለትንሹ ጎረቤታቸው ልጅ እጅን አውለበለበለት።
“ከእኛ ጋር መጫወት ትፈልጋለህ?”
“አይ! በነገራችን ላይ ፤ የበለዶ ሰዎች ለህፃናት ናቸው” ፤ ብሎ ሁልቱንም እጆቹን በኪሱ ውስጥ እየከተተ ሄደ።

(p. 14)

Un peu déçu, Junior retourne vers ses camarades.
– Tu avais raison, Nina, il n’est vraiment pas gentil.
– Venez, on va terminer notre bonhomme de neige, les encourage Dino.

ትንሽ ቅር ብሎት፣ ጁኒየር ወደ ጓዶቹቹ ተመለሰ።

“ትክክል ነበርሽ ኒና፣ እሱ በእውነት ጥሩ ልጅ አይደለም። ”
“ኑ፣ የበረዶ ሰዋችንን ሰርተን እንጨርሰው፣” ዲኖ አብረታታቸው።

(p. 16)

– Oh, comme il est beau ! s’émerveille la petite fille.
– Mais il lui manque quelque chose, constate Dino en se grattant la tête.

“ኧረ እንዴት ቆንጆ ነው! ” ትንሿ ልጅ ተደነቀች።
“ግን የሆነ ነገር ይጎድለዋል” ይላል ዲኖ ጭንቅላቱን እያከከ።

(p. 19)

– Oui, je sais : un bonnet pour le protéger du froid, réplique Junior en enlevant le sien pour le mettre au bonhomme de neige.
– Ah ! voilà ! maintenant, il est prêt pour affronter le froid ! se réjouit Nina, ce qui fait rire ses amis.
Pendant que les trois amis s’amusent, Junior remarque que le petit voisin les observe de sa maison, l’air triste.

“አዎ! አወቅኩት፣ ከ ብርድ ለመከላከል የሹራብ ቆብ ” ጁኒየር መለሰ፣ የራሱን ቆብ አውልቆም ለበረዶው ሰው አለበሰው።
“ኦህ! በቃ ! አሁን ቅዝቃዜውን ለመጋፈጥ ዝግጁ ነው ! ” ኒና ደስ አላት፣ ይህም ወዳጆቿን አሳቃቸው።
ሶስቱ ጓደኛማቾች እየተጫወቱ እያለ፣ ጁኒየር ትንሹ ጎረቤቱ ከቤቱ ሆኖ እነርሱን እደሚመለከታቸው አስተዋለ፤ ያዘነ ይመስላል።

(p. 20)

– Atchoum ! Atchoum ! fait Junior.
Au même moment, sa maman le rappelle :
– Junior, il faut rentrer maintenant, avant que tu ne tombes malade.

“ሀንጥሴ! ሀንጥሴ!” ጅኒየርን አስነጠሰው።
ወዲያውኑ እናቱ “ጅኒየር፣ ከመታመምህ በፊት አሁኑኑ ወደ ቤት ግባ”።

(p. 22) Une fois à la maison, Junior se réchauffe près de la cheminée avec ses parents. Il leur raconte ce qui s'est passé avec le voisin.
– Tu crois qu'il ne nous aime pas, maman ?
– Mais non, mon chéri, peut-être qu'il était intimidé par vous trois. J'ai une idée ! Et si on faisait des mikatés pour les lui apporter ?
– Hmmm, mon goûter préféré ! Trop bon !

አንዴ እቤቱ ከገባ በኋላ፣ ጅኒየር የእሳት ምድጃውን ተጠግቶ ከወላጆቹ ጋር እሳት ይሞቃል።
ከጎረቤታቸው ጋር ምን እንደተፈጠረ አጫወታቸው።
"እማማ፣ የማይወደን ይመስልሻል?"
"በፍፁም፣ የኔ ውድ፣ ምናልባት እናንተን ሶስታችሁን ፈርቶ ይሆናል። አንድ ሃሳብ መጣልኝ! ምንመሰለህ ሚካቴ ሰርተን ብንወስድለትስ?"
"እምም፣ ተወዳጁ መክሰሴ! በጣም ጣፋጭ!"

(p. 24) Plus tard dans la journée, Junior et sa maman se rendent chez leurs voisins. Il se hausse sur la pointe des pieds et sonne à la porte. Une dame vient leur ouvrir.
– Bonjour, voici Junior et je suis Kimia, sa maman. Nous sommes vos voisins d'en face.
– Bonjour, Junior, bonjour, Kimia. Moi, c'est Sophie et lui, c'est Arthur. Tu dis bonjour ? Mais Arthur se cache derrière sa maman.
– Entrez, ne restez pas dans le froid.

በዚያው ቀን ቆየት ብሎ፣ ጁኒየርና እናቱ ወደ ጎረቤቶቻቸው ሄዱ። በእግሮቹ ጫፍ ቆሞ የበሩን ደውል ደወለ። አንዲት ሴት በሩን ልትከፍትላቸው መጣች።
"እንደምን ዋላችሁ፣ ይህ ጁኒየር ይባላል፣ እኔ ደሞ ኪሚያ ፣ እናቱ ነኝ። ከመንገዱ ማዶ ያለን ጎረቤቶቻችሁ ነን።"
"ሰላም ጁኒየር፣ ሰላም ኪሚያ። እኔ ሶፊ እባላለው። እርሱ ደግሞ አርቱር። ሰላም በላቸው? "አርቱር ግን ከእናቱ ኋላ ተደበቀ።
"ግቡ፣ ብርዱ ላይ አትቁሙ" ።

(p. 26) – Miam, c'est trop bon ces petites boules ! s'exclame Arthur, qui oublie sa timidité en dévorant les beignets qui lui ont été offerts.
– Ce sont des mikatés, un goûter de mon pays d'origine et ma maman fait les meilleurs.

"እም፣ እነዚህ ትናንሽ ኪሶች በጣም ጣፋጮች ናቸው! " አለ ጮክ ብሎ አርቱር ፣ አይናፋርነቱን ረስቶ የቀረበለትን ጮርናቄ ጎረስ ጎረስ አደረጋቸው።
" እነዚህ ሚካቴ ይባላሉ፣ ከትውልድ አገሬ የመጣ የከሰላት ምግብ ነው እናቴ ደሞ ስትሰራው ምርጥ ነው" ።

(p. 28) – Pourquoi tu n'es pas venu jouer avec nous, tout à l'heure ? demande Junior.
– Parce que j'avais peur que vous vous moquiez de moi, dit Arthur.
– Mais pourquoi dis-tu ça ? lui demande Junior, surpris.
– Là où j'habitais avant, je n'avais pas de copains. Les autres étaient méchants avec moi, avoue Arthur tristement.

"ቅድም ለምን መጥተህ ክእኛ ጋር አልተጫወትክም ? " ጁኒየር ጠየቀው።
"እንዳታሾፉብኝ ፈርቼ ነው።" አርቱር መለሰ።
"ግን ለምን እንዲህ ትላለህ ? " ጁኒየር በመገረም ጠየቀው።
ከዚህ በፊት በኖርኩበት ቦታ፣ ጓደኞች አልነበሩኝም። ልጆቹ ለኔ ክፉ ነበሩ..." አለ ባዘነ ድምፅ።

(p. 30) Junior est désolé pour Arthur. C'est alors qu'il lui demande :
– Est-ce que tu veux bien être mon ami ?
Arthur accepte avec un grand sourire.

ጁኒየር ስለ አርቱር አዘነ። ከዚያም እንዲህ ሲል ጠየቀው፣
"ጓደኛዬ መሆን ትፈልጋለህ ? "
አርቱር በታላቅ ፈገግታ ጓደኝነቱን ተቀበለው።

(p. 32) Jouons ensemble !
Observe les deux images. Trouve les sept différences et entoure-les sur la deuxième image.

አብረን እንጫወት !
ሁለቱን ሥዕሎች ተመልከቱ። ሰባቱን ልዩነቶች ፈልጉ እና በሁለተኛው ሥዕል ላይ አክብቡበት።

(p. 34) Solution

መፍትሄ

Traduction : Senait Yoseph ሰናይት ዮሴፍ ተወልደ

Coordination des traductions :
Interbiblio
www.interbiblio.ch
info@interbiblio.ch